# GRUBHUB

## የማዳረስ አጋርን አካውንት ከአገልግሎት ውጭ የማድረግ ፖሊሲ

የGrubhub ማድረስ አጋሮች ደንበኞችን ከሚወዷቸው ነጋዴዎች ጋር ለማገናኘት አስፈላጊ ናቸው፣ የእኛም ዓላማ በአስተማማኝ እና በብቃት ለማድረስ በመሳሪያዎች፣ በእውቀት እና በንብረቶች እርስዎን መደገፍ ነው።

በGrubhub፣ ግባችን የእኛን መድረክ ለሚጠቀሙ ሁሉ ደህንነቱ የተጠበቀ እና አስደሳች ተሞክሮ እንዲኖራቸው ማድረግ ነው። ይህንን ለማሳካት እንዲያግዝ፣ Grubhub ሁሉም ተጠቃሚዎች የእኛን መድረክ ከመድረሳቸው በፊት የ Grubhub መድረክን ለመጠቀም የሚያስፈልጉ መስፈርቶችን እና ሁኔታዎችን ያስቀምጣል። ከGrubhub ጋር በንቃት ማድረስ ለማስቀጠል ከምን አይነት ድርጊቶች ወይም ባህሪያት መራቅ እንዳለባቸው ያውቁ ዘንድ ለማድረስ አጋሮች መመሪያ ለመስጠት ተስፋ እናደርጋለን።

የዴሊቨሪ አጋሮች አግባብነት ባለው የማድረስ አጋር ስምምነት ውስጥ በተቀመጡ ደንቦችና ሁኔታዎች ይገዛሉ። በተጨማሪም፣ የእርስዎ Grubhub አካውንት ከአገልግሎት ውጭ እንዲሆን ሊያደርጉ ከሚችሉ እርምጃዎች ወይም ባህርያት መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፦

1. የደንበኛ ነጋዴን ወይም የሶስተኛ ወገን ደህንነትን የሚነኩ ወይም ኢኮኖሚያዊ ጉዳት የሚያስከትሉ እና ከGrubhub መድረክ ጋር የተቀራኙ ድርጊቶች ወይም ባህሪያት፦

    - የደንበኛን፣ የነጋዴን፣ የሶስተኛ ወገን፣ የGrubhub ወኪልን ወይም ሰራተኛን አካላዊ ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥል ማንኛውም ድርጊት ወይም ባህሪ። ለምሳሌ፣ አንድ የአስረካቢ አጋር አንድን ደንበኛ ወይም የነጋዴ አጋር በአካል ካጠቃ፣ ከባድ በደል በመሆኑ አስቸኳይ የሆነ ማቦዘን ያመጣል።

    - በደንበኛ፣ በነጋዴ፣ በሶስተኛ ወገን ወይም በGrubhub ላይ ኢኮኖሚያዊ (የገንዘብ) ጉዳት የሚያደርስ ማንኛውም ድርጊት ወይም ባህሪ። ለምሳሌ፣ ማንኛውም የገንዘብ ማጭበርበር ተግባር፣ ሆን ተብሎ የማድረስ ጊዜ ወይም ርቀት አላግባብ መጨመር፣ ትዕዛዝ ወይም ሌላ ነገር መስረቅ ወይም ማበላሸት፣ ወይም የንብረት ውድመት ማድረስ የመሳሰሉ በመሆን ከባድ በደል በመሆኑ አስቸኳይ የሆነ ማቦዘን ያመጣል።

    - ደንበኛ፣ ለነጋዴ፣ ለሶስተኛ ወገንን ወይም Grubhubን የሚያስፈራራ፣ የሚተነኩስ ወይም የሚበድል ድርጊት ወይም ባህሪ። ለምሳሌ፣ በአንድ ሰው ደህንነት ላይ ማንኛውም የቃል ዛቻ፣ ከባድ በደል በመሆኑ አስቸኳይ የሆነ ማቦዘን ያመጣል።

2. አልኮል ዴሊቨር የሚያደርጉ ከሆነ፣ [የGrubhub የአልኮል መጠጦች ማድረስ ፖሊሲ] አለማክበር፣ የተቀባዩን ዕድሜ ወይም የስካር ሁኔታ ሳያጣሩ አልኮል ማድረስን ጨምሮ።

3. የማንነት ማጭበርበር፣ እንደ የማድረስ አጋር መረጃን ማጭበርበር፣ የሌላን ሰው ማንነት መያዝ፣ የተባዛ አካውንት መፍጠር፣ አካውንትዎን ያለፈቃድ ለሌላ ሰው ማጋራት፣ የግል መረጃን አለማረጋገጥ ወይም የራስ ያልሆኑ የግል መረጃዎችን ወይም ሰነዶችን ማስገባት።

4. ሁሉም የማድረስ አጋሮች የሞተር ተሽከርካሪ መዝገቦችን እና የወንጀል ታሪክን መገምገምን የሚያካትቱ መደበኛ የቀድሞ ታሪክ ፍተሻዎች እንዲደረግባቸው መስማማት አለባቸው። ትክክለኛው የብቁነት መመዘኛ እርስዎ ባደረሱበት ቦታ እና በመረጡት የመጓጓዣ ዘዴ ላይ የተመሰረተ ሊሆን ይችላል። ከማናቸውም

GRUBHUB

የሚመለከታቸው የክልል እና የአካባቢ ህጎች በተጨማሪ፣ በቀድሞ ታሪክ ፍተሻዎች ላይ ተመስርተው አካውንት ከአገልግሎት ውጭ እንዲሆን የሚያበቁ አንዳንድ ምክንያቶች እነዚህ ናቸው፦

- በቅርብ ጊዜ የተፈጸሙ ከባድ ወንጀሎች
- በቅርብ ጊዜ የተፈጸሙ ከባድ የወንጀል ጥፋቶች—ወሲባዊ ጥቃት፣ በህፃናት ላይ የሚፈጸሙ የወሲብ ወንጀሎች፣ ግድያ/ነፍስ ግድያ፣ ሽብርተኝነት፣ ህገወጥ የሰዎች ዝውውር እና እገታን ጨምሮ
- ገና በመታየት ላይ ያሉ ማናቸውም ከባድ የወንጀል ክሶች
- ባለፉት 2 ዓመታት ውስጥ የተከሰቱ ከአንድ በላይ የእንቅስቃሴ ደንብ ጥሰቶች ወይም አደጋዎች
- መጠጥ ወይም ዕፅ ወስዶ ማሽከርከር፣ ሞገደኛ አሽከርካሪነት ወይም ገጭቶ ማምለጥ የመሳሰሉ የቅርብ ጊዜ ከባድ የማሽከርከር ደንብ ጥሰቶች

5. የአካውንት ጥሰቶች። “የአካውንት ጥሰት” ማለት ነጋዴዎች፣ ተመጋቢዎች እና Grubhub ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የሚያሳድር አካሄድ ወይም ባህርይ ነው። የአካውንት ጥሰት ከተፈጸመ፣ በGrubhub የአሽከርካሪዎች መተግበሪያ በኩልና በኢሜይል አማካይነት ማሳወቂያ ይደርስዎታል። ጥሰቱን በመተግበሪያው በኩል የማየትና የማረጋገጥ ዕድል ይኖርዎታል። ጥሰቶች የሚያበቁበት ጊዜ ያላቸው ሲሆን፣ ከ90 ቀናት በኋላም ከአካውንትዎ ይወገዳሉ። በ90 ተከታታይ ቀናት ውስጥ 3 ጥሰቶች ከተፈጸሙ፣ አካውንትዎ ከአገልግሎት ውጭ ይደረጋል፣ እርስዎም ወደ መተግበሪያው መግባት አይችሉም። አንድ አካውንት ከአገልግሎት ውጭ ሊደረግባቸው ከሚችሉ ባህርያት መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፦

- ትእዛዞችን አለመፈጸም - ትእዛዞችን መቀበል እና ማዳረስን ለመፈጸም ፈቃደኛ ባለመሆን ምክንያት ነጋዴው እና ደንበኛው ትእዛዙ እንዲዘገይባቸው ወይም እንዲሰርዙት ማድረግ
- ነጋዴዎች ሳይዘጉ እንደተዘጉ ምልክት ማድረግ - ነጋዴው የስራ ቦታው ክፍት ሆኖ ትዕዛዞችን መቀበል ቢችልም ነጋዴውን እንደዘጋ አድርጎ በመተግበሪያው ውስጥ ሪፖርት ማድረግ
- ትእዛዞችን ከተቀበለ በኋላ አለማድረስ/ወደ ተሳሳተ ቦታ ማድረስ - ትዕዛዞችን ወደተሳሳተ ቦታ በማድረስ ወይም ትእዛዞች/ዕቃዎችን በመስረቅ ትእዛዞችን አለማጠናቀቅ
- የተቀበልካቸውን ትዕዛዞች ለማንሳት ወይም ለማድረስ መዘግየት - ትዕዛዙን ከተቀበለ ወይም ከነጋዴውን አድራሻ ከሄዱ በኋላ ወደ ነጋዴው/ደንበኛ አለመሄድ
- ከመጠን በላይ የተከፈለባቸው ትዕዛዞች - በደንበኛው ከታዘዙት በላይ ብዙ እቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን በGrubhub አሽከርካሪ ካርድ ላይ መግዛት
- መገኛ ቦታን መደበቅ/ማሳሳት - በመተግበሪያው ላይ እርስዎ ዝግጁ በሆኑበት ጊዜ ትክክለኛ አካባቢዎን መደበቅ ወይም ማሳሳት
- የዴሊቨሪ ሂደትን ማጭበርበር - ወደ ነጋዴው ቦታ ላይ መድረስን በተመለከተ እንደዚሁም ትእዛዝን ስለመረከብና ማድረስ በተመለከተ የተሳሳተ መረጃ መስጠት

# GRUBHUB

- የተሳሳቱ ፎቶዎች - ሆን ብሎ እውነታን ለማዛባት በመፈለግ ትክክለኛ ባለጉዳይን ወይም ጥራት የማይወክሉ ፎቶዎችን መስቀል ወይም ማቅረብ

- ትዕዛዞችን ያለምክንያት መሰረዝ - የስረዛ ክፍያን በሐሰት ለማግኘት በማሰብ ትእዛዞችን በስህተት መሰረዝ

- መታወቂያ ስካን አለማድረግ - ስካን የሚያስፈልገው ማድረስ በሚከናወንበት ወቅት ደንበኛው መታወቂያውን ስካን እንዳያደርግ በተከታታይ መሞከር

- ሁሉም እቃዎች እንደማይገኙ አድርጎ ምልክት ማድረግ - ትእዛዝን ለመሰረዝ እና የማድረስ ክፍያ ለማግኘት በማሰብ ሆን ብሎ ሁሉንም የግዢ እቃዎች እንደማይገኙ ምልክት ማድረግ

- ከከፈሉ በኋላ ግዥን መሰረዝ - ከከፈሉ በኋላ ዕቃዎቹን ሳይመልሱና ተመላሽ ገንዘብ ሳይቀበሉ የግዥ ትዕዛዞችን መሰረዝ

- አልኮል አለመመለስ - አንድን ትእዛዝ ለደንበኛው ማድረስ ካልተቻለ አልኮልን ወደ ነጋዴው አለመመለስ

- የማድረስ ፒን አለመጠቀም - በሚጠየቅ ሰዓት የማስረከቢያ ፒን አለመጠቀም።

- ተመጋቢዎች፣ ነጋዴዎች፣ ሌሎች ሶስተኛ ወገኖች ወይም Grubhub ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድር ወይም አሉታዊ ተጽእኖ እንደሚያሳድር የሚያሰጋ ማንኛውም ተመሳሳይ ባህርይ።

ይህ ከላይ የተጠቀሰው አካውንት ከአገልግሎት ውጭ የሚደረግባቸውን የተለመዱ ምክንያቶችን ይዘረዝራል፣ ነገር ግን፣ የማድረስ አጋሩ የGrubhub ማድረስ አጋር የአጠቃቀም ውልን ጨምሮ፣ ከGrubhub ጋር የገባውን የውል ስምምነት ማንኛውንም ደንቦች፣ ወይም ማንኛቸውም አግባብነት ያላቸው ሁኔታዎች ወይም ፖሊሲዎች ከጣሰ፣ የGrubhub መድረክ መዳረሻን ሊያጣ ይችላል። Grubhub አካውንት ከአገልግሎት ውጭ ስለመደረጉ ማሳወቂያ ይ